## ምዕራፍ ፫ ትግሬ (ዐይን)፤

ጥንታዊ የኢትዮጵያ ጥበብ ያለበት የታወቀው ያአኵስም ቤተ መንግሥት የነበረ በት ዝነኛው ጠቅላይ ግዛት ትግሬ ነው ። ሥርወ መንግሥቱም የመጣ ከዚያው ነው ። ሕዝቡ ብዙ ዘመን ስለኖረበት መሬቱ ተበልቷል ፤ ብሎም አንበጣ በእያመቱ በይወረው ሀገሩ ራሱን እንደሚችል የታመነ ነው ።

ለመድኃኒት የሚበጀው ለጤና ተስማሚው አሽንል የሚባለው ያሞሌ ልመደው ጨው የሚገኘው በእንደርታ ብቻ ነው ። በእየቆላው የሚረባው ፍየል ከእገሌ ሀገር ጋራ ይወዳደራል አይባልም እጅግ ብዙ ሲሆን ጣዕሙም ግሩም ነው ።

ዐይን የተባለበት ምክንያትም ሕዝቡ በመጀመሪያ በዚያ ስለገባና በሥልጣኔም ቀዳ ሚ ስለሆነ ነው ።

ዋና ከተማው መቀሌ ይባላል

አውራጃዎቹ ፡ ሀ) መቀሌ ፡ ለ) ዓጋሜ ፡ ሐ) ተምቤን ፡ መ) ዐድዋ ፡ ሠ) ሽሬ ፡ ረ) አኵ ስም ናቸው ።

ወሰን በሰሜንና በምሥራቅ ኤርትራ ፤ በምዕራብ በጌምድር ፡ በድቡብ ወሎ ይዋ ስኑታል ።

ዓይንሽ ምድረ ትግሬ በጣም የጠራው
አልፎ ሃጁን ሁሉ አነሆለለው ።
ጥንቱንም ተብሏል በአባቶቻችን
ግጥምን በሚያወርዱት በሚያውቁት ቅኔን
ዓይንሽ እየጠራ የሚያመጣውን ሰው
ስንቱን በወጨፎ ብዮ ልጨርሰው ።
በጣም አደጋ ነው የሴት ዓይን ጥራት
ከሩቅ ቦታ ጠቅሶ ያመጣል ጣላት ።
ያይንሽን ኩል ዐይቶ ደግሞም ጥራቱን
ሊያገባሽ ፈለገ ጐረምሳው ጣሊያን
ቱርክ እንኳ በዐቅሙ ሊወሽምሽ ደርሶ
ጆሮሽን ነካክቶ ጡትሽንም ደሳሶ
እጁን ስሞ ሄደ ቤቱን ተመልሶ
በአሸጋሪ ሁነሽ በጠራው ዓይንሽ
ጥሩ ቦታ መርጠሽ መነጥር ሳትሽ
አቀማመጥሽን ያሳመረልሽ
ያይንሽ ጥራቱ ነው እናት ልንገርሽ
ሽፋሽፍትሽ መረብ ዘምራና ጥራሪ
አሻግሮ ለሚያይሽ ከቶ እንደምን ታምሪ ።

ብሌኔሽ አኵስም ከጥንት የታወቀ
በዓለም ሕዝቦች ዘንዳ በጣም ተደነቀ
የብሌኔሽ ውበት ተጽፏል በሐውልት በታሪብ መቅድም
አይረሣም ከቶ እስከ ዘለዓለም ።
በአኵስም አደባባይ መሳፍንት ሲሰፉ
በእልፍ አጀብ ተከበው ነገሥታቱ ሲያልፉ ።
ጀግናው ወታደርሽ ሲከማች ለሰልፉ
ሊቃውንቶችሽም መጻሕፍት ሲጽፉ
ትመለከቺ ነበር ሁሉን በየረድፉ ።
በልብ አስተውሰሽ በዓይንሽም ዐይተሽ
በአንጐልሽ አስበሽ በቃል ተናግረሽ
በአንደበት አጉልተሽ ሰው ዐወቀልሽ
ዘላለም አይጠፋም ይህ ትልቅ ታሪክ
ሲነገር ይኖራል በዓለም ዘንዳ ሡርክ
ዓይንሽ ቢመረመር በታሪክ ሐኪም
ቅምጥም አልተገኘ እንኳንስ ሕማም ።
እናቴ ልንገርሽ የገረመኝን
አለመድከሙ ነው ይህን ሁል ዘመን
ሲነድፍ ሲፈትል ነጭ ሐር አስማምቶ
ለልጆቹ ብሎ ሌሊት ተጐልቶ
ደግሞም ከዚህ በላይ የታሪክ መጻፍ
ሲያነብ የኖረ ነው አንድ ቀን ሳያርፍ
ቀኑንም ሲሰፋ ላዳን ቀኍናውን
ይመስል ነበረ የሚጠፋብን
አሁን ብናየው ግን በጣም ገረመን
ባገራችን ሰማይ እንዳጥቢያ ኮከብ
ሲያበራ ይታያል ለዚህ ዓለም ሕዝብ
ጠጉርሽ ተበጥሮ እንዲህ ያማረው
ወንበርሽ ቁብ ብሎ ሰውን ሚያስቀናው
ሽንጥና ወገብሽ ጥበቡ ኩታሽ
ያማረ በዓይንሽ ነው እኔ ልንገርሽ ።
ሰሎሞን ገረመው ዓይንሽን ስላየ
አብሮሽ ለማደርም በጣሙን ተሰየ
አስቦም አልቀረ ቀንና ሌሊት
ተገኘ ምኒልክ በአንድ ቀን ምሼት

የምኒልክ ልደት የሰሎሞን ፍቅር
በዓይንሽ ነው የመጣ ልብሽ አይጠርጥር
ዓለምን ለማየት ዓይንሽ ቢወረወር
ግብጻዊ ደንግጦ ማሰ አሉ መቃብር
ዐረብ የመን ሽሽ እስከ ሕንድ ድረስ
በግርማ ቢታየው ታላቁ ንጉሥ
ዐዔ ካሌብ ታጥቆ ካይንሽ ላይ ተነሥቶ
ተመልሶ መጣ ዐረብን ድል ነሥቶ
ዓይንሽ ተደነቀ አሻግሮ ሰው ሲያይ
ዐረብና የመን ደግሞም ግብጽ ላይ ።
ከጦር ተራራ ላይ ዓለምን ቢያውጽ
ከበታቹ ሆኑ የመንና ግብጽ
እንደምን ይገርማል ያይንሽ ደኅና መሆን
ታሪክ ስታነቢ ይህን ሁሉ ዘመን ።
ሰዎቹ ይላሉ ማንበብ ዓይን ያጠፋል
እናት ያንችው ግና እያደር ያበራል
<u>ኢትዮጵያ</u> አታንብ የሚሉ ሰነፎቹ ናቸው
ዝም ብለህ አትስማ አይረባም ምክራቸው
ዓይንን የሚያጠፋው አቶ መጠጥ እንጂ መቼ መጽሐፍ ነው
አይረባም ወሬያቸው አትቀበለው ።
ልብ አርገህ አትስማ ዋጋም የለውና
ቁም ነገርም አይደል ነው እንጂ ስንፍና
የጫጉላ እንቆቅልሽ ተረብና ቢልታ
መሠረት የሌለው የልጆች ጨዋታ
ጊዜ እያሳለፈ ቤትን የሚፈታ ።
ሰነፍን ጓደኛ አጥና ብትለው
ዋዘኛን ኰበሌ ተማር ብትለው
ፊዘኛን ኩታራ ቀጥል ብትለው
አውደልዳይ ጐረምሳን አንብ ብትለው
የመንደር አፊሌን ከልስ ብትለው
ጊዜን በቍም ነገር ማዋል ሲጨንቀው
ሚሰጥህ ምክንያት በጣም ብዙ ነው ።
ኰረዳ ገምርራ ማጥናት ሲጨንቃት
የልቧን ስንፍና የልቧን ሀኬት
ውስጡን እያወቀች የሸሸግሁ መስሏት

ማንበብ ዓይን ያጠፋል ሚሉ ምክንያት
ታወራለች ባፏ ያላንዳች ዕፍረት ።
ይህ ስሕተት ነው ብለህ ሰነፍ ብትነግረው
አፍህን ያስይዝሃል እንኳን ልትረታው
በጣም ወግ ዐዋቂ ሞገደኛ ነው ።
በሕይወትህ ድንገት እንዳያታልልህ
ሥራውና ግብሩን በል ስማ ልንገርህ ።
በጣሙን አጥብቆ ለመረመረው ሰው
ሰነፍና ፈሪ ባህላቸው አንድ ነው ።
ማልዳ ተነሥ ቢሉት ይበርዳል ይላል
ቀን እንዳያጠና ፀሐይ ይሞቃል
ሌትም እንዳያነብ ዐይኑ ይጠፋል
ኳስ እንዳይጫወት እግሩ ይቈስላል
ልሥራ አይልም እንጂ እንመልከት ሲል
ላንዱ ቈንጥ ሲያወጣ ሌላውን ሲያቄል
ከሁሉ ሲተርብ ዘመኑ ያልፋል ።
ተማሪ ቤት ትቶ ቢሆንም ገበሬ
መና ቢቀር እንጂ አያገኝም ፍሬ
የግብርና ሥራ እንደ ምታውቀው
የጀግንነት መሥዋዕት የሚጠይቅ ነው ።
ማለዳ ተነሥቶ በሮቹን አውጥቶ
እሣር ወይንም ጭድ የሚበቃ ሰጥቶ
ክረምት እንደሆነም በሸታ አሠማርቶ
በአንዛብ ጨፌውን እስኪጠግቡ አብልቶ
በቋሚ በጮጮ በትልቅ ግሬራ
ላሞቹን አራክቦ ሁሉንም በተራ
አመዳይ ሐሩሩን ብዙውን መከራ
ሲሠራ ይኖራል አንዳችም ሳይፈራ
የገበሬም ምሽቱ ያለም ሁሉ እናት
ከሱ ጋራ ውላ ቀኑን ስትቃትት
ስታጭድ ስትጐለጒል ያላንዳች ዕረፍት
ደግሞም ተቀምጣ ታድራለች ሌሊት ።
ወጧን እንደሠራች እንጀራዋን ጋግራ
ሰትፈትል ስትነድፍ መብራቷ ሲበራ
ቍጭ ብላ ታድራለች ሌሊቱን ስትሠራ ።

እንደዚህ አይደሉም ሰነፎቹ ግና
ክረምት ይርዳሉ ሲመጣ ደመና
በጋውንም ደግም ፀሐይ ሲመታቸው
ያለከልካሉ ላብ እየዋጣቸው
ብርዱ ሲነካቸው ይጨማተራሉ
ነፋሱ ሲያያቸው ይኰፋተራሉ
ቈፈን ሲይዛቸው ይጨባበጣሉ ።
ይህ ሁል መከራ እንዳይደርስባቸው
ለቆ ይከርሙና ባልጋ ላይ ተኝተው
ሳይዘሩ እየቀሩ ክረምቱን በሙሉ
በመኸር ያውድማ ለማኝ ይሆናሉ
   እንደዚህም ሁሉ ላየው በልቡና
በጣም ያናድዳል የተሜ ስንፍና
መብራቱን አብሮቶ ሌት እንዳያጠና
ልቡ ይጨነቃል ሲመጣ ፈተና
እኔ ግን እናትህ ሰነፍ አልወድም
ሌት ተቀን ብዬ ነው የማጠናውም
ብዙዎች ነበሩ የማይቈጠሩ
ከኔ ጋራ ሁነው ታሪክ የሚማሩ
ተግቶ የተማረ ሌሊቱን ያጠና
ምስክር አገኘ አለፈ ፈተና
ቀኑን ሲያውደልድል ሌሊቱን ተኝቶ ሳይሠራ የኖረ
አልቦ ተቀብሎ ከዚያው ክፍል ቀረ
እኔም በትጋቴ ከጓደኞቼ ጋራ
አገኘሁ ምስክር በታሪኬ ሥራ ።
ደረጃዬም ነበር የታሪክ መምህር
ከባልትና ጋራ የሚያስተባብር
ብዙዎች ይሉታል መምህርን ዶክተር
ደግሞ ፕሮፌሰር ምለውን መሪ ጌታ
በጣሙን ካወቀ የክፍሉን ሐተታ
እኔም በዚሁ ትርጉም መሪጌታ ተብዬ
ገባሁ ቤቴን ማታ ስፈነጥዝ ውዬ
የስንፍናን ጉዳት የትጋትን ጥቅም
በራሴ ነገርሁህ የቀረ የለም ፤
ሚያግርህ እንዳለ ጠይቅ ልንገርህ

አስረጅ መምህር አጥተህ እንዳይቸግርህ ።

<u>ልብ</u> ድግሪ ያገኘሽው ያለፍሽው ፈተና
ምን ክታብ ጽፈሽ ነው በታሪክ ጕዳና

<u>ኢትዮጵያ</u> ከብዙው እንግልጋ ጽፌ ከያዝሁት
መርጬ ሠራሁኝ የአኵስምን ሐውልት
ያኵስም ከተማዋ ያኵስም ሥልጣኔ
በጥንታዊነቱ ሰጠኝ ኵራት ለኔ
ከክርስቶስ በፊት ብዙ ዘመናት
የሠራሁት ሐውልት በብዙ ብልሐት
ዛሬ ያኰራኛል በሰው ልጆች ፊት
ሐውልቱ ረዥም ነው በጌጥ የተዋበ
በሐረግ ያጌጠ በጽሕፈት ያበበ
ታሪኩ የበዛ ጥንታዊ ከተማ
ሁሉ ያደነቀው በዓለም የተሰማ
የክታቡን አርእስት ሐውልት አረግሁና
ጽፌበት ነበረ ሌላውንም ባልትና ፤
ጽሕፈትና ሥዕል ሐረግና ድጉስ
አንድነት መቀመም ብዙ ዕፀው ለፈውስ
ወጥ ሥራና ፈትል ጠላ መጠንሰስ
ጠጅ በሰፌው መጣል መጋገር እንጀራ
ኵታ ጥንግ ድርብ ደግሞም ጥበብ ሥራ
ጠላት የሚያሳፍር ወዳጅ የሚያኰራ
ይህን ሁሉ አንድነት ባቀርብ በተራ ፤
ተመርቄ መጣሁ ከሽልማት ጋራ ።

<u>ልብ</u> እናቴ ንገሪኝ ጓደኞችሽን
ካንቺ ጋራ ሁነው በታሪክ ወገን
መምህር የሆኑትን አልፈው ፈተናን ።

<u>ኢትዮጵያ</u> የኔ ባልንጀሮች በክፍል የሚማሩ
ብዙ ምሥራቃውያን አብረውኝ ነበሩ
በጥሩ ሥራቸው ማስታውሳቸው
ውል ውልም የሚለኝ ንግግራቸው
የሚከተሉቱ ወይዛዝርት ናቸው ።
ቀርጤስ ፍልሰጥኤም ግብጽ ኢየሩሳሌም
መወዳደር እንጂ ሚቀድማቸው የለም
ሕንድና ባቢሎን ሶርያና ቻይና

በዓለም የታወቁ ባሉሙሉ ዝና
ይማሩ ነበሩ ታሪክ በጉብዝና
አሁን ከዚህ በላይ የተጠቀሱት
በዓለም ላይ ሲጀመር የታሪክ ትምህርት
ቀዳሚ ነበሩ ሁሉም በኅብረት
ደግሞ እነሱ ናቸው ከሁሉ በፊት
ምርቅ የተባሉ በታሪክ ዕውቀት
ከሁለተኛው ክፍል ከኛ ለጥቀው
ፍኒቅና ግሪክ ሮምም ሁነው
ከካርታጎ ጋራ በጣሙን ተግተው
ይማሩ ነበረ ሌት ተቀን ብለው ።
ሌላ ሰው አላውቅም እኔ ከነሂ ሌላ
እኛ ከወጣን ነው ይህ ሁሉ የፈላ ።

ልብ　　እናቴ ተመስገኝ በጣም ደስ አለኝ
ባልንጀሮችሽን ስለ ነገርሽኝ
የሠራሽው ሁሉ ታሪኩ ገባኝ ።
አብረውሽ ሲሠሩ በታሪክ አዝመራ
ስላልነገርሻቸው የልብሽን ሥራ
ያንች አሜት ጉባኤ የተደረገለት
ሰምቻለሁና የሁሉን ዕውቀት ።
ታሪኩን ዐውቃለሁ የሁሉንም በፍጹም
ምንም ነገር የለ አንቺን የሚያደክም ።
ጓደኛው ለእገሌ ማነው ይላል ሰው
ይገመታልና ሰው በጓደኛው ።
እነሱ ከሆኑ የጥንት ጓደኞችሽ
አትድከሚ እናቴ እገልጣለሁ ብለሽ
ተሰባኝ ተረዳሁ ትርጓሜው የሥራሽ ።
　　አንድ ነገር አለ በጣም ሚጨንቀኝ
የጽሕፈትሽ መምጫው ሥሩ ቸገረኝ ።
ዛሬ ማልዳ ሂጄ ካንቺ ጉረቤት
ሰዎች ሲሉ ሰማሁ እኛ አስተማርናት ።
ዐረብና የመን ፍኒቅና ሳባ
ያወሩ ነበረ በዚሁ ስብሰባ
ጽርእም ላከችና አባ ሰላማን
የሆኄዋን ተራ ነገርኋት አለን ።

ይህንን ሰምቼ ስለ ተቸገርሁ
ወዳንች መጣሁኝ እኔም እየሮጥሁ ።

<u>ኢትዮጵያ</u> በል ዝም ብለህ አድምጥ የምነግርህን
እንድመልስልህ የጠየቅኸውን ።
ባለቤት ሲያቀለው ሲለው አልባሌ
የትም አይቀበል ጐረቤት አሞሌ
እንደዚህም ሁሉ የገዛ ልጆቼ
በደንብ አሳድጌ ሁሉን አስጠንቼ
ጽሕፈቱን ሐረጉን ሥዕሉን አሳይቼ
ብረቱን አውጥቼ ወርቁንም አንጥሬ
ሐውልቱን ቀርጬ መልኩን አሣምሬ
እንዳላስፋፋሁኝ ዕውቀት በሀገሬ
ዕውቀትና ሥርዓት ሁሉን አስተምሬ
ሠርቼ ቀጥቼ ያሳደግኋቸው
ልጆቼ ሰነፉ በጐብዝናቸው
ሠርቶ መብላት ጠልተው በጭሩ ታጥቀው
ባልጋ ላይ ተጋድመው ዋሉ ተኝተው ።
ዕውቀት ተቀበረች መጣ ድንቁርና
ራስ ትጋት ሙቶ ተሾመ ስንፍና
የካህናት ንጉሥ ቅናት ነገሠና
ጠቢቡ ሲያወራ የጥበቡን ዜና
ይቈጠር ጀመረ ከታላቅ ብልግና ።
በዚህ ጊዜ ሁሉ ያበው ረጀት
በዓለም የታወቀው የመጣው ከጥንት
ይቈጠር ጀመረ እንደ መጃጃት ።
ብልሁ ተዋረደ ሰነፉ ከበረ
አቃቂር ነገሠ ታሪክ ተቀበረ
ጥበብ የሚያውቅ ሁሉ በጣም ተነወረ ።
ጥበበኛ ሁሉ ሲሠራ በደኅና
ስም ያወጣ ጀመር ሰነፍ ቊጭ አለና
ትርጉሙ ሳይገባው በቊሙ ሲቃጅ
ሁሉን በጠቅላላ ሰየመው ባለእጅ
ትርጉሙን ሳያውቀው ለሰው ስም አወጣ
ጠቢብ ባለጅ ሲሆን ራሱ ቁማጣ
መሆኑን ሳያውቀው እንዲያው ቀባጠረ

በመንፈስ ተነሥቶ እውነት ተናገረ ።
ደግሞም ከፋፈለው ሽማኔና ቀጥቃጭ
ፋቂ ደበን አንሣ ድሬ ሠሪ አንጣጭ
አርሶና አበራይቶ አጭዶ ባበላው
አባቱን ገበሬ አለው ና አስቲለው
የማር ጌታ አናቢ ጠጅ የሚጥለው
ሆነ ገተም ገሪ እሱም በሙያው ።
ወተትና ሥጋ የሚሰጠውን
ወንድሙን ሰደበው እያለ ዘላን
ጻፊም ተሰደበ እንደዚሁም ሣይ
ጠልሰም ጠልሳሚና አንት መጥፎ ጠንቋይ
ሁሉም ተሰደበ ጠቢብ አንጥረኛ
ከዚህ ማት የሚያድን አልተገኘም ዳኛ ።
በጉርምስናቸው መሃለኛው ዘመን
ሰነፉ ልጅ ሲሰድብ ሠርቶ ሚያበላውን
እንግዶቹ መጥተው ከጐረቤታችን
ጠቢብ ሥራ ሂዶ አግኝተው ሰነፉን
በጭዋነት ኰርቶ ልብስ ለብሶ ሲያዩት
እሱ ማይወደውን ሥዕልና ጽሕፈት
ብረት መሥራትና ሌላም ጥበባት
ተግባረ እድንም ያገርን ብልሃት
የሁሉን የትመጣ ቀርበው ጠየቁት ።
ወዲያው ያሰላስል ይተክዝ ጀመረ
እኛ ነን እንዳይል ልቡ ተቸገረ
ጽሕፈት እኛ ጀመርን ብሎ ቢናገር
ጠንቋይ ሚባል ሆነ ያባቶቹ አገር
ብረት አቀለጥነ ብሎ ቢናገር
ጋሻውን ሰጐድነ ብሎ ቢናገር
መሣሪያም ሠራነ ብሎ ቢናገር
ጀንዲም አለፋነ ብሎ ቢናገር
ነጭ ሐር ሠራነ ብሎ ቢናገር
ሌሎችንም ጥበብ እንዲሁ ቢያከብር
ቀጥቃጭ ሚባል ሆነ ያባቶቹ ዘር ።
ደግሞም ከዚህ በላይ ሁኖ በትሕትና
ጥበብን ቢያሞግስ ቢሰጣት ልዕልና

የሚገለጥ ሆነ የራሱ ስንፍና
ሞልቶ ከተረፈው ከናቱ ባልትና
ከጭዋነት በቀር ምንም አያውቅና
በስንፍና ምግር ቈርጦ የሠራው
እንዳይናድበት መከበር ጐጆው
ሰበሰበ ሐሰት የውሸት ደገፋ
ከዱር ትዕቢት ገብቶ ስሜን እያጠፋ ።
እንዲህ ነገራቸው የልቡን ፈጠራ
አታውቅም እናቴ እንዲህ ያለ ሥራ
ጽፈትን ደረሱ ሌሎች ጠንቋዮች
ብረትን አፈሉ መጢ ፈለሾች
ጠቢብ ከሽማኔ የውጭ አገር ሰው
ወሰን ማናደርገው መሬት የሌለው
ባሀገራችን ላይ የባለ እጅን ሥራ
ሌት ተቀን ቢሠራ መቸም ሳያባራ
ይኖራል በመጥፎ ሀገሬን ሲያስጠራ ።
በጭዋነት ኰርቶ ይህን ቢነግራቸው
ወዲያው ተመለሱ እየደነቃቸው ።
በቅድሙ ተረት እንደ ተባለው
ሥልጣኔ አሞሌን ጌታው ቢያቀለው
አይቀበለውም መቸም ባለዕዳው ።
እንደዚህም ሁላ ይህን መልስ የሰሙ
ቤታቸውን ገቡ እየተገረሙ ።
በዚህ መልስ መሠረት ሞኝ ሰው ስላገኙ
እኔ አሰተማርሁ ሊሉ ብዙዎች ተመኙ
ይወልደዋል ካለ ይመስላል አይገድም
ይለጥፋት ጀመር በመሰል ሁሉንም
እጅና እግሩን ቈርጠው ፊደሉን በተራ
ይመስላል ይላሉ ተስማምተው በሴራ ።
በአዋልድ ተጽፎ ሕዝብን የሚያውክ
ይህን የሚያስረዳ ልንገርህ ታሪክ ።
ይህን ዓለም ፈጥሮ ረቂቁ አምላክ
ከሰማይ መላእክት ስለተሠወረ
ፈጣሪ ፍለጋ ነገድ ተሸበረ ።
ረብሻውን ያየ ሳጥናኤል መላክ

እኔ ፈጠርሁ ብዬ እስኪ ልመለክ
የሚል ሐሳብ ይዞ ሁሉንም ሊገዛ
ፈጣሪው እኔ ነኝ ጫጫታው አይብዛ
ብሎ አዋጅ ነገረ ፈጣሪ ቢጠፋ
መላእክትም ሰምተው ይህነን በይፋ
እኩሉ ሲሸበር ሌላው ሲሰግድ
ከመሃል ቤት ደርሶ ገብርኤል ሚባል ወንድ
ወዲያውኑ ሻረበት አዋጁን ባዋጅ
በያለህበቱ ቁመህ ጠብቅ እንጅ
እስክናውቀው ድረስ ፈጣሪያችነን
አትስገድ ለፍጡር ብሉን አትሁን
ብሎ ቢያጥናናቸው ሊቃናት በሙሉ
ፈጣሪ እስኪናገር በአማን ቍመው ዋሉ
እንደዚህም ሁሉ ዓለሙ ሲሸበር
መሬት እስኪናገር እርጋ ማለት ነበር ።
በመልሱ እንደሰጠው መስሎ ቢታይ ሞኝ
ያ ሰነፉ ልጅ በጣም ማያውቀኝ
ፈጠርናት ለማለት ሁሉም ከጀሉኝ
ሐሰት እንደሆነ የሳጥናኤል ወሬ
ይህም እንደዚያው ነው መቸም የለው ፍሬ ።
ሰዎች ሲጠይቁህ እንዳይልህ ወንጃ
እሰጥልሃለሁ ለሁሉም ማስረጃ
ከሁሉ ጥንታዊ በዓለም ላይ ያለው
ፊደሌ እንደሆነ ሊቆች መርምረው
ተስማምተው አድረዋል አንድነት ሁነው ።
ግብጽ ሽቆ ሰትፈልግ ባቢሎንም ገል
ሳባ የዕንጨት ሳንቃ ስትቈረቍር ሳል
የፈረስ የፌቆ የበግ የፍየል
ብራናዬን ፍቄ ዳምጬ በውል
አረገው ነበረ ጽሕፈቱን ኰለል ።
አስተማርሁኝ ብላ ፊኒቃ እንዳትኰራ
አይገጥምም ፊደሌ ምንም ከሷው ጋራ ።
በዐሥረኛው ዘመን ከጌታ በፊት
ዕብራውያን አመጡ ብዙ መጻሕፍት
ወዲያው ተረጐሙት ወደ ግዕዝ ቋንቋዬ

ለማንበብ እንድችል እንደ ልቡናዬ
ከዚህ ኋላ መጥተው ዐረብና ሳባ
አስተማርናት ቢሉ ከልብም አይገባ ።
ከዚያ ፊት ባይኖረኝ እንደነሱው ቃል
ሌላ በመፈልሰፍ ከምነሆልል
እወርሰው ነበረ የነሱን ፊደል
ትልቁ ሰባኪ ፍሬ ምናጦስም
ሃይማኖት ነው እንጂ ቋንቋ አላስተማረም
ልማድ አልለወጠ ተራ አላፋለሰም
እንኳንስ ይህንን ትልቁን ነገር
በጉባኤ ቢሰብክ ግዝረት እንዲቀር
ታቦትም በዑደት እንዳይከበር
በኦሪት ሕገጋት ሕዝቡ ስላመነ
መሰለው የከዳ አረሚ የሆነ ።
ዳር እስከ ዳር ሕዝቡ አንዴ ቢናወጥ
ዕለቱን ጀመረ ስብከት ሊለውጥ
የሆሄውን ተራም ሊያደርገው እንግዳ
ጽፎ አቅርቦ ነበር የሱን አቡጊዳ
ደግሞም እንዲማሩ በሆሄው አንጻር
አልፋ ቢታ ብሎ ጽፏቸው ነበር
ሊያስጠናኝ ፈልጎ የጽርእን ፊደል
በጣም ደክሞ ነበር በተቻለው ሁል
ዳሩ ግን ባልፈልግ የራሴን መጣል
አንዝ አረግሁና እሱ የሰጠኝን
እቀጥል ጀመረ ጥንታዊ መንገዴን ።
እሱ ግን ያመጣው የፊደል እንግዳ
መሥመሩ ጠማማ ወዲህም ወልጋዳ
ስለሆነ ለልጅ ተሎ ማይረዳ
አዲሱ የመጣው ፊደል አቡጊዳ
ተብሎ ይጠራል መጥፎ የልጅ ዕዳ
ይህ ነው ታሪኩ እውነተኛውማ
የቀረው ሐሜት ነው የጠላት ፍልሰማ ።

ልብ አሁን በነገርሽኝ አመስግናለሁ
ነገር ግን አንድ ነገር እጠይቀሻለሁ
ካይንሽ ላይ ሚገኘው የአኵስም ሐውልት

አሮጌ ገንዘብም የነበር ከጥንት
በሳባና፣በጽርእ የተጻፈበት
ማስረጃ ነው አሉኝ ሰዎቹ ተላንት ።
በግዕዝ ያልተጻፈ ለመረመረው
በሐውልትሽ ጊዜ ፊደል ባይኖር ነው
ብለው አፈን አሉኝ ይህንን ጠቅሰው ።

ኢትዮጵያ

ጥርስ ብቻም አይደል መንጋጋም ያስቃል
የዚህ መልስ ቀላሉ እንደምን ይጨንቃል ።
የዚህ መልስ ይህ ነው ልቡናህ አይበባ
በምዕራብ አገር ጽርእ ባረብ አገር ሳባ ።
የዚያ ዘመን ቋንቋ በመሆናቸው
ሲዛወር ነጋዴ እንዳይቸግረው
የውጭ አገር ንግድ እንዲሆን ቀላል
ጻፍሁኝ በገንዘቡ የውጭ ፊደል ።
የጽርእ ቋንቋ ጻፍሁኝ በሐውልቱ ላይ
የሩቅ አገር መጢ በቀላል እንዲያይ
ዕውቀቴ እንዲገርመው ላለም እንዲወራ
ዝናው እንዲነገር የሠራሁት ሥራ
ማስተምረው ትምህርት በዓለም እንዲዘራ ።
በገንዘብ በሐውልት የተጻፈበቱ
የሳባና የጽርእ ይህ ነው ብልሃቱ
ፊደሌን ሚያስረዳ ጥንታዊነቱን
ተጽፎ ይገኛል በዚያኑ ዘመን
አንድነት ከሳባ ደግሞውንም ከጽር
በገንዘቡ ምስል በሐውልቱ ሥር ።
የዘመንህን ውሰድ ለዚህ አብነት
ዛሬ ቤት ሲሠራ ደግሞውንም ሐውልት
ፈረንሳይ እንግሊዝ እንዲጻፍበት
ይህኑ ምሳሌ ሊያስረዱ ሚችሉ
ባሥመራና ባዲስ ብዙ ሕንፃዎች አሉ ።
በውጭ ቋንቋዎች ምን ሲጻፍ ቢውል
አስረጂ ለመሆን መቼ ይችላል ።
ያሁን ዘመን ሥራ ለጥንቱ ማስረጃ
ሊሆንህ ይችላል ልብህ አይበል ወንጃ ።
ዛሬ በባልትና የወልድኳቸው

ጥንታዊ ሙያዬን በመርሳታቸው
አዲስ ነው ይላሉ ለጠያቂያቸው ።

**ል ብ**

በጣም ረዥም ነው እመ ታሪክሽ
ደግሞውንም ብዙ ዓይነት ጥንታዊ ሙያሽ
ማልዳ ጀምሬ ነው ጽሒፈት የጻፍሁኝ
ብለሽ ስትኳሽ እንደ ነገርሽኝ ።
ጥንታዊ ጥበብሽ ላለሙ ሲተርፍ
ምነው አልቈየንም ለኛ በጽሑፍ ።

**ኢትዮጵያ**

የዚህ መሰናክል እንቅፋት የሆነው
ሰንፍናዬም አይደል ሌላ ምክንያት ነው
የያዝሁትን ጥበብ ከአሪት በፊት
ያረሚ ነው ብለው በእሳት አጠፉት ።
ወንጌል ስትሰበክ ኦሪት ሞተችና
ይጥፉ ብላ አዘዘች የሙት ፍልስፍና
ሊቁ ተሰደደ ታሰረ በግፍ
ስለተገኘበት ያለፈው መጽሐፍ
ከሺ ዓመት በኋላ ጒዲት ተነሣች
የኦሪት የናቷን ደሟን መለሰች ።
የተቀበረችው እናቷ ልትመጣ
ሕዝብ ተገረፈ ዓለም ፀየ ጣጣ
አወጀች በዓለሙ ሊቃውንቱ ሁሉ
እንደ በግ ይታረድ አይማር በሙሉ
ሐዲሳት መጻሕፍት በእሳት ይቃጠሉ ።
ታሪክ ይህ ነው ብሎ ለመጭው ዘመን
ያጠናውንና ባይኑም ያየውን
ለሰው እንዳያተርፍ ምላስና እጁን
ቍረጥ ብላ አዘዘች የሊቃውንቱን ።
መጽሐፍ ይያዝ አለች በያገሩ ዙሪ
አቃጥላ ጨረሰች ገዳሙን በተራ
ቤተ ክርስቲያኑንም በመላ በርብራ
አመድ አረገችው በጥበብ ሳትራራ
እንዲህ እያደረገች አርባ ዓመት ገዛች
የጥበብን ሽታ ከዓለም አጠፋች ።
ከሞተች በኋላ ብዙ ሠራሁኝ
ቅኔና ፈለክም ዜማም ደረሰሁኝ

ግራኝ ኋላ መጥቶ እስኪያጠፋብኝ
ስልምና ነገሠ ጠፋ ክርስትና
ልማድም ታሠረ እንኳን ፍልስፍና
ክርስትና ቢናድ የጥበባት ግንብ
ዓለሙን ወረሰው ድንቍርና ዝንብ ።
እሱም ያለ ምሕረት እንደ ጉዲት ሁላ
ቤተስኪያን መጻሕፍት አጠፋ በሞላ ።
ደግሞም ከዚህ በላይ ሥነ ጽሑፌን
ግብጻዊ ዝንጀሮ ሚባለው አቡን
ባይረዳውና ቋንቋው ባይገባው
ሰብስቤ ሰብስቤ ከንቱ አደረገው
ይሾሙ ጀመረ በሱ ዘመናት
ያልተማሩ ሰዎች የዱር አራዊት
ዛፍ መጋለብ ሳይሆን ሰውን ለመምራት
ባራዊት ተከቦ የተማረ ሰው
ከንጉሡ ዘንዳ ማን አደረሰው
በዕውቀቱም ምክንያት ታሥሮ ተገረፈ
ሰው እንዳይጠጋው በአቡን ተለፈፈ
በዕውቀት ቢበልጣቸው አሥረው በቅናት
ለንጉሡ ሰጡት ሊቁን ካህናት
በሐሰት ሲያወሩ ወንጀሉን በጥብቅ
ንጉሥ አያከብርም ይኸ መናፍቅ
ሕዝቡን ያስተምራል ክህደትና ዐመፅ
ጃውሳ ነውና የማይገሠፅ
ይህነን ቢሰማ ንጉሥ ተናደደ
ምንም ሳይጠይቀው ይሰደድ ፈረደ ።
የበኽር ልጇ ዕውቀት ከሱ ጋራ ሁና
አብራው ተሰደደች ዓለም ሆነ ዱና
የጀመሩት ሥራ ፈለክ ፍልስፍና
እነሱ ቢሄዱ ይኸው ቀረ መና
ደግሞም አቶ ጠቢብ እንዲሁ ተከሰሶ
ሲቧዝዝ ይኖራል ከመሬቱ ፈልሶ ።
ሌሎች ሊቃውንትም እንዳይናገሩ
መገረፍ መስቀል መስደድን ፈሩ
ዕውቀት ቀና ብላ ሰትታይ ባገሩ

ሰው እንዳይጠፋበት ይቀብሩ ጀመሩ ።
በቅናት ስትጠፋ ጥንታዊት ዕውቀት
ድንቍርናን ደግሞ ፍርሃት ወለዳት
የሰው ነገር ሰሚ ሲነግሩት ማይሰማ
በነገሠ ጊዜ በጥንቱ ከተማ
ሥልጣኔ ጠፋ ድንቍርና ለማ ።
በቃሌ አጠናሁኝ እሰኪችል ጉልበቴ
ጥበቤንም ዘጋሁ ያዝሁኝ በአንደበቴ ።
በሰፊው ማይገኝ ጥንታዊ ጽሕፈቱ
ስንፍናዬ አይደለም ይህ ነው ምክንያቱ ።
ባንደበት አጕልተው በቃል ተናግረው
ጥንታዊ ጀግኖቼ ባይኔ ሳያቸው
በመርከብ ተሰፍረው ግመል ተጭነው
በእግር መንገዳቸው ከሰላም ደርሰው
በሰናር በረሃ ወደ ግብጽ ወርደው
ረመጬትና ሐሩር ታግሠው
የሀገሩን ቋንቋ በጣም ተምረው
መጽሐፍ ተረጒሙ ወደ ቋንቋቸው ።
የቀድሞ አባቶችህ ይህንን ሲሠሩ
መጻሕፍት መመርመር ዙረህ በየደብሩ
ያንት ፈንታ ይሁን ልጄ ሆይ በምሩ ።
ምንም ቢዘንብባት የውሸት መከራ
አንዳንድ ሊቅ ጽፏል ማንንም ሳይፈራ
በሐይቅ በየዋሻው በየገዳማቱ
ብትፈልግ ይገኛል በሰፊው ጽሕፈቱ ።
ፈልገህ ብታገኝ ብታነበውማ
ያስተምርህ ነበር ታሪክን በሴማ ።

ልብ    አመስግናለሁ ስለታሪሽ
ግን እጠይቃለሁ ስለ ሕይወትሽ ።
ምንድር ቢበላ ነው ዐይንሽ የጠራው
ከብት ያልረገጠው ምንጭ መስሎ ሚታየው ።

ኢትዮጵያ    በራያ ባዘበ በሰፊው በረት
ሲጋፋልኝ ያድራል ብዙ የቀንድ ክብት
ከግመሉ ጋራ በእንደርታ በጋጤ

የበግ ጠቦትና የፍየል ወጠጤ ።
በቦራ ስላዋ ላንድ ሰው ፍየል
ሺህ ሺህ ቢኖረው ብዙም አይባል ።
ኵራትም አይደለ ፍየሏን ማራከብ በጊቱን መላግ
ወፍራሙ ወተቷ ቀቤው በጣም ደግ ።
የፍየሌን ወተት ይገኘ በግሬራ
በለስ እየጨመርሁ ሲመስል እንጌራ
አቅርቤ እበላለሁ በፋጋ ተራራ ።
በእንደርታ በተንቤን ባጋሜም ኅሮዬ
ጠጅ ሚሆን ማር አለኝ እንደ ልቡናዬ ።
በጣም የታወቀው ያኵስም ነጭ ጤፍ
ሽምብራውም ግራር ሰው ማያሳልፍ
ይችላል ቀለቤን ከሽመት እንዳርፍ ።
አዲያቦና ሽሬ ወደዋና ውቅሮ
ያበቅላል ብዙ እህል ዐይነቱን ማን ቈጥሮ ።
የራያ ያዘቦ ያዲያቦ ማሽላ
እሸቱና ንፍሮው ደግሞም መልካም ጠላ
ሰውን ያስደስታል እንደ ማር ወለላ ።
ወተትና ማሩን እህልና ቅቤውን እየገመትሁ ባይኔ
ከያለበት መጥቶ እበላለሁ እኔ ።
የዘራሁትን ሰብል ካልበላው አንበጣ
አላቀናም እንጂ ለሽመት አልወጣ ።
አብዛኛውን ጊዜ ውኃ ምጠጣው
በእርኮቴ እየቀዳሁ ከበረሃ ነው ።
ወዲያው አፈላና በፀሐይ እሳት
ስጠጣው ጤና ነው የለውም ቍርጠት ።
የምጠርበው አሻል በትግሬ በእንደርታ
ጥሩ መድኀኒት ነው ለብዙ በሽታ ።
እየሌና አሞሌ ታላቅ ልመደው
ዓለም ያደነቀው አለኝ ጥሩ ጨው ።
ዐይኔ ዳፍንት የለሽ በጣም ጥሩ ነው
በጨለማ ሲሄድ ማነው የሚያክለው ።
ሌሊት ተነሥቼ መንገዴን ስሄድ
እንኳንስ እንቅፋት አይመታኝም ጉርድ
ሌሊት ተነሥቼ ከጠላት ስዋጋ

በዐይኔ ጥራት ነበር የተጠበቀ አልጋ ።
እስከሁን ነገርሁህ የሁሉን ኑፋቄ
በል አሁንም ንገረኝ እንዳለህ ጥያቄ

ልብ
አመሰግናለሁ በጣም ደስ አለኝ
ስለልጅነቴ ምንም ሳትንቂኝ
በልብሽ ሳትዪ ሰው ያቀለኛል
ስለገለጥሽልኝ ታሪክሽን በሙል ።
እኔም እንደ ዐቅሚ መወድስ ሰጥቼሽ
እንሰነባበት ሥራ እንዳላስፈታሽ ።

## መወድስ ።

ኢትዮጵያ እምነ ዓለም ተደነቀ
አንድነት ሁኖ ዛሬስ፡ በሠራሽው የታሪክ ሥራ
ታይቶታልና በግልጥ፡ ዐይንሽ ሰማዩ ሲጠራ
ዜማውን ሲያወርድ ለሕዝብ፡ ያሬድ የድጓ መሪ ጌታ፡ ዐዋቂው ደብተራ
ካሌብም ወደ የመን
በመርከቡ ይዞ ሲሰፍ፡ ወሰን የሌለውን ጭፍራ
ዐይንሽሂ ያጥቢያ ኮከብ ለመላው ዓለሙ ሚያበራ
የምሥራቅን ሕዝብ ሰብአ ሰገል፡ አመጣቸው እየመራ ።
ተወልዷልና ውብት፡ አምላክ አገው ዕዝራ
በገጽኪ ኀለ እንስሳ፡ ዓለሙን ሊያድን ከመከራ ።

## ምዕራፍ ፩ ኤርትራ ጆሮ ።

ከከሰላ እስከ ፈረንሣይ ሱማሌ ድረስ በቀይ ባሕር ዳር ለዳር እንደ መቀነት የዘረው ጠቅላይ ግዛት ኤርትራ ነው ። ሁለቱ ወደቦቻችን ምጥዋና ዐሰብ የሚገኙበትና ከውጭው ዓለም ጋራ የምንገናኝበት የባሕር በራችን ስለሆነ ጆሮ ተብሏል የኤርትራ ዋና ከተማ አሥመራ ናት ።

ወሰን፡ በምሥራቅና፡ በሰሜን፡ ቀይ ባሕር፡ በምዕራብ ሱዳን፡ በደቡብ በጌምድር፡ ትግሬ የፈረንሳይ ሱማሌ ይዋሰኑታል ።

አውራጃዎች፡ ፩ ሐማሴን (አሥመራ)፡ ፪ አከለ ጉዛይ ዓዲ ቀ.፡ ፫ ሠራዬ (መንደ.)፡ ፬ ሰንሒት (ከረን)፡ ፭ ሳሕል (ናቅፋ) ፮ ባርካ (አቁርደት)፡ ፯ ሰምሃር (ምጽዋ)፡ ፰ ደንካል አሰብ።

ልብ
በኤርትራ ጆሮሽ ሁሉንም ሰምተሽ
በዐይንሽ አስተውለሽ በልብሽ መክረሽ
ታስቀምጪ ጀመር ዕውቀት ባንጐልሽ ።
ጆሮሽ እየሰማ ሁሉን ቢያጠናው
ሠለጠነ ዓለሙ ገሠገሠ ሰው ።
ከምሥራቅ ከምዕራብ ሰምተሽ ጥበብን

ወዲያው ትይዝ ያለሽ የሚጠቅምሽን ።
ጆሮሽ እንዲህ ሁኖ ለዕውቀት የተጋው
ንገሪኝ እማዬ እንዴት ቢሆን ነው ።

ኢትዮጵያ

ሁሉን ለማዳመጥ ጆሮዬ ቢተጋ
ለሥራው ለግብሩ ሰውነቴም ሠጋ
መጽሐፉ ያዝዛል ዓለሙን በመላ
ለመስማት እንዲፈጥን መቼም ሳይል ችላ ።
ለመፈጸም ብሎ አምላክ ያለውን
ጆሮዬ ይሰማል ተግቶ ሌት ተቀን ።
በምሥራቅ እናረብ ሕንድና ጃፓን
ፋርስና ባቢሎን ጽርና ሚደን
ግብጽና ቆጵሮስ ኢየሩሳሌም
በምዕራብም ደግሞ ፈረንሳይ ሮም
ሲያወሩ ሲያጠኑ ስለ ሥልጣኔ
እንደ ሰማኋቸው አደረግሁት ለኔ
ሌሎቹ ሲያወሩ በሩቅ ከሰማሁ
በበነጋው እኔ እሠራዋለሁ ።
ሞክረው ነበረ ማይችላቸውን
ጆሮዬን ሊደፍኑ ቱርክና ጣሊያን ።
ጠቅጥቀው ወትፈው በሰም ባርነት
የሚሠሩትን ግፍ እንዳልሰማበት ።
ግን ፈጣሪ ባይል አምላክ ባይፈቅደው
ተደፍኜ እንዳልቀር እንደ ታሰበው
ቱርክ የወተፈውን መግዛት ሰፈፍ
ያባ ታጠቅ ካሣ ጀግንነት ወናፍ
አመድ አደረገው አንዳችም ሳይተረፍ ።
የተረፈውንም አባ ታጠቅ ካሣ
በጦርነት እሳት አቅልጦት ተነሣ
ደግሞም እንዳልሰማ ባርነት ሰምን
ጆሮዬን ቢወትፍ ጉረምሳው ጣሊያን
በዚህ ዘመን ንዶ እሳታችን መላ
አቅልጦ ፈጀበት የሠራውን ሁላ ።
ጀግኖች አወጡልኝ ባርነት ኩኬን
ከሩቅ እሰማለሁ የሚወራውን ።
ባሕር ተሻግሬ እንደልቡናዬ

ሂጀ እጫወታለሁ ከሩቅ ጓደኛዬ
ደንቄሮም አልባል ከሰማ ጆሮዬ ።
ልቡናው እያለ ማን ነው እኔን ሚያማ
ጆሮዬ ተክፍቶ በነጻ ተሰማ
ያ ቄሻሻ ሰፈፍ ባርነት ይዞኝ
እንደዚያ ሲጨንቀኝ መስማት ቸግሮኝ
እሰይ እልል እያልሁ ልንገር ለሚያውቀኝ
ጆሮዬ ሊሰማ ተከፈተልኝ ።
ልዞረው ዓለሙን ሁኜ በመርከብ
ሰንደቅ ዓላማዬ ሰትውለበለብ ።
በባሕር ልንሳፈፍ ልበል ሽርሽር
በሰፊው መርከቤ ልቀበል አየር ።
ለመስማት ከቻልሁኝ ቀርቶ ድንቁርና
የሚያየኝ ሰው ሁሉ ያከብረኛልና ።
በሩቅ ምሥራቅ በኵል ሕንድና ጃፓን
በምዕራብ እንግሊዝ ፈረንሳይ ጀርመን
ሰምቻለሁና የሠሩትን ሁሉ
ሂጄ አመጣዋለሁ በመርከቤ ሙሉ ።
በጣሙን ጤነኛ ዋናተኛ ሆንሁ
ጆሮዬ ተከፍቶ ባሕር ተገባሁ ።

ልብ በምሥራቅ በምዕራብ ያላንዳች ዕረፍት
ጆሮሽ የሰማውን የዓለምን ዕውቀት
በሥራ ለማዋል ደግሞ እንዳይጠፋሽ
ሁልጊዜም ለማሰብ በምን ትሠሪያለሽ ።

ኢትዮጵያ ልነግርህ ነበረ አንተ ሳትጠይቀኝ
ካመጣኸውማ በል ነቅተህ ስማኝ ።
ምሰማውን ሁሉ ሊቁ ሲያስተምር
ደግሞም አልፎ ሃጁ ለሰው ሲናገር
ማጠናበትና ምክልስበት
ሠራሁኝ ጠንክሬ ብዙ ትምህርት ቤት ።
ባሥመራ በከረን ባቁርደት ከተማ
ያለው ትምህርት ቤቴ ዝናው የተሰማ ።
በምጥዋ ወደብ ደግሞም በዓዲቀይ
የሠራሁት ሕንፃ ልብን የሚያሰይ ።
ያ ኃይለ ሥላሴ አሥመራ ቢመጣ

ድንቍርና ጠፍቶ ሀገር ነጻ ወጣ ።
ካንደኛ ደረጃ እንዳላልፍ እኔን
ወስኖኝ ነበረ የኢጣልያ ዘመን
በልቤ እንዳጠናው እንዳውቀው ሁሉን
እርነት ሊያወጡኝ መጡ አግዓዝያን ።
በአግዓዝያን ትጋት ነጻ ከወጣሁ
ደንቆሮ እንዳልባል እጠናዋለሁ ።
ታላቁ መስፍኔ ልዑል መኰንን
ጥበብ ይሸልማል የሚያኰራውን
ከተከፈተልኝ አንደኛ ደረጃ
ደግሞም ሁለተኛ ሰውን ሚወረጃ
ስንፍና ባሥመራ መኖሩንም እንጃ ።
ሀኬት እንዳይገባ በኃይል ጸጸራት
እዋጋዋለሁኝ ሁኜ በኅብረት ።
ድንቍርና ደግሞ ከቤቴ እንዳይደርስ
እምለዋለሁኝ ቤተ ጊዮርጊስ ።
ብልግና እንዳይረግጣት ሀገሬን በሙሉ
በአሥመራ ሚገኙት አዋልዱ ሁሉ
ሊት ተቀን ጠንክረው ተግተው ይማራሉ ።
እንዲለማ ባህሌ እንዲሰፋ ሥራ
አብረው ይማራሉ ስላምና አማራ
ጀሮዬ እየሰማ ዐይኔ ያየውን
ለማስታማር ብለው ለሰው መምህራን
ማሠልጠኛ ገብተው ዐቅድና ስልቱን
ሲማሩ ይታያል ተግተው ሌት ተቀን ።
ነጮች ሚሠሩትን የጥበብ መንገድ
እኔ እጠናዋለሁ በተግባረ እድ
የጆሮዬን ትጋት ዐይተው ሥራዬን
አሥመራ ደረሱ ግሪክና አርመን ።
ታሪኬን የሰማ ስዊድን ጉብል
ሊሰብከኝ ደረሰ ይዞልኝ ወንጌል ።
ተፈጥሞ ሄደ በመኰንን ላይ
አቶ ድንቁርና የሀኬት ሰላይ
ምጥዋን እንዳይደርስ ሀገር እንዳያይ ።
ሕንፃው የሚያስደስት ለሚጐበኝ ሰው

ውብቱ ያማረ የደስ ደስ ያለው
አለኝ ትምህርት ቤት በየከተማው
በዚህ ሁል ገብቼ ያላንዳች ዕረፍት
አዲስ አጠናለሁ እንኳንስ መርማት
ደግሞም ከዚህ በላይ በደብረ ቢዘን
ተግቼ እማራለሁ ሐዲስ ብሉይን
ጆሮዬ ካጠና ከፈለገ ዕውቀት
ተግተው ሚያስተምሩ ጽኑዕ ሃይማኖት
አሉኝ ደስ ይበልህ ብዙ ገዳማት
በደቀ መሐረ ከረን መንደፈራ
አለኝ ብዙ አኪም ቤት አምሮ የተሠራ ።
አዲቀይ ባረንቱ ደግሞም አቁርደት
አሉኝ ሆስፒታሎች ለሰው ልጅ ሕይወት ።
መድኀኒት ቤት ሠራሁ በአውራጃ ወረዳ
በአጥቢያው በቀበሌው በመንደር በዱዳ
ኤርትራዊ ሁሉ በቅርቡ እንዲረዳ ።
በዚህ ሁሉ ስሠራ በታላቅ ትሕትና
ልቤ ተደስተ አገኘሁኝ ጤና ።

<u>ል ብ</u> ለትምህርት ለጤናስ በጣም ትጉ ነሽ
ለመመላለሻስ ምን መንገድ አለሽ

<u>ኢትዮጵያ</u> ካንዱ ዱዳ ሁኜ ወዳንዱ መንደር
በስፋልት ጐዳና ነው የምንሸረሸር ።
በመኪና መንገድ በባቡር ሐዲድ
ከምጥዋ አሥመራ ባየሁ ስጓደድ ።
ዕንቅፋት ሳይመታኝ እሾኽ ሳይወጋኝ
ደንጊያ ሳያግደኝ ጠጠር ሳይነካኝ
ከሥመራ ከሰላ እገባለሁኝ ።
ሽርሽርም ሲያምረኝ ወደ ዓዲግራት
እፈስበታለሁ በሰፊው አስፋልት
ዓዲቀይንና ደግሞም መንደፈራ
እፈስበታለሁ ዕንቅፋት ሳልፋራ ።
በጽዳት በውበት ያማረችውን
ዕያት ከተማዬን ይችን አሥመራን
ባማራ ምሳሌ የተባለው ከጥንት
ስም ይወጣ ከቤት ይቀበል ጎረቤት

ስለደረስላት ላሥመራ ከተማ
በጽዳት በውበት ዝናዋ ተሰማ
አሥመራ አስደሰታት ተብሎ ሲፈታ
እሰማ ነበረ በግዕዙ ሐተታ
እኔም ካፋፏ ላይ ቁጭ ብዬ ባያት
አእምሮዬ ረካ ልቤ ሲደሰት
በመንገድ በጽዳት በውኃ በመብራት
ባቀማመጥና በሕንፃ ውበት
አሥመራዬን ከቶ ማነው የሚያክላት
ከተማዋን ሁሉ እንደ ጐበኘህ
በል እስቲ ንገረኝ ምነው ስሜትህ

ል ብ ስሜቴን ለመግለጥ ስለዚች ከተማ
በል ንገረኝ ብለሽ ከጠየቅሽኝማ ።
ፎቋን ሰገነቷን አደባባይዋን
መንገዷን ሕንፃዋን ውኃ መብራቷን
ልቡና የሚሰይ ውበት ጽዳቷን
አካሄዷንና አረማመዷን
በትምህርት መገሥገሥ ቅልጥፍናዋን
የጸጥታ ኑሮ ሕግና አመሏን
ዙሬ ጐበኘሁት ዐየሁት ሁሉን
እንኳን ጥፋትና የለውም እንከን
ሌቱን ሲሄድ ያድራል ጋሪና መኪና
ጐረምሳም ሽርሽር ያላንዳች ብልግና
ማስተዳደሪያው ሕግ በጣም ጸንቷልና
በጣሙን ይገርማል ይደንቃል ልቡና
ይዛ መገኘቷ አመል ከቁንጅና ።

ኢትዮጵያ እንዲህ ነኝ እናትህ በምሥራው ሁሉ
በጣም ያደስታል ሰውነት በሙሉ ።
በምዕራብ ሲጨወት ከሰማሁትኝ
ሁሉንም ሠራሁኝ አንድም አልቀረኝ

ል ብ ብፅዕቲቱ እናቴ በጣም ልባይ ነሽ
ጆሮሽ የሰማውን አለመርሣትሽ
ማላውቀው እንዳለ ደግሞ ከዚህ ሌላ
ንገሪኝ እናቴ ልረዳው በመላ ።

<u>ኢትዮጵያ</u> ልማረው ማለትህ በጣም ደግ ነው
ረሥቼው ነበር የምጥዋን ጨው ።
ጨዌን እሠራና ምጥዋ ወርጄ
ዐድለዋለሁኝ እንዲበላው ልጄ ።
አፈልጥ እጠርብና በምታውቀው ኃይሌ
ላለም አቀናለሁ ልመደው እሞሌ
ለሰው ልጅ አሸበ ለክብትም እዬሌ
ጣፋጩን ወረቀት አምባዛና ጋርሣ
ስዝቀው ባየኸኝ የምጥዋን ዓሣ
የቀይ ባሕር ዓሣ ለቀመሰው ሰው
በጣም ይጣፍጣል ወደርም የለው ።
ሲወጣ ለሚያየው ልብ የሚያስደስት
የጨው ማጣፈጫ አለኝ ጥሩ ዘይት ።
በብረታ ብረት በጣም ሀብታም ነኝ
ብርና ቆርቆሮ ብዙ ወርቅ አለኝ ።
ጥጡን በየቈላው እመዛዝንና
ስፈትለው ባየኸኝ ባዲሱ መኪና ።
ጥጤ ሲፈነዳ ኮከብ ሚመስለው
ሌሊቱ እንዳይጨልም መስኩን አበራው ።

<u>ልብ</u> እመ ስለውቀትሽ አወራሽ ሁሉን
ደግሞ እስኪ ንገሪኝ ከሲሳይ ወገን ።

<u>ኢትዮጵያ</u> ከሲሳይም ወገን ብዙ ፍሬ አለኝ
ባለም ገበያ ላይ የሚያስከብረኝ ።
የከረን ብርቱካን ሚመስለው ጉልቻ
ራት ይሆንሃል ብትይዘው ለብቻ
በአዲስ አበባ ላይ በውድ ይሻጣል
ያሥመራ ሙዝ አለኝ ብሎ ሚያታልል ።
በከረን ሚዘራው የለውም አምሳያ
ትርንጎ ሚመስለው ጣፋጩ ፖፖያ ።
በነፋሲት መንገድ ሚበቅለው በለስ
ለቀመሰው ሁሉ አለው የደስ ደስ ።
መቼውንም አላዝን ቢቀር አዝመራው
ራቤ ይጠፋል በለሴን ሳየው
ኮክና ትርንጎ ደግሞም በኸረ ሎሚ
አለኝ ብዙ ፍሬ ለሰው ዘር ጠቃሚ ።

በገበያ ሲሸጥ የፍሬዬ ሰብል
አልፎ ሃጃን ሁሉ ያነሆልላል ።
ከብቴን አረባለሁ በቄላ ቄላው
ወተትና ሥጋ ልጄ እንዳያምረው ።
ያለኝን ባጭሩ ይኸው ነገርሁህ
ደግሞም ከዚህ ሌላ ምነው ጥያቄህ ።
ል ብ  ስላጨዋወትሽኝ ተመስገኝ እናቴ
መወድስ ሰጥቼሽ ልሂድ ወድቤቴ

መ ወ ድ ስ ።

ምድረ ኤርትራ ጆሮሽ ከሩቅ የሚሰማ
ሲገረፍ ሰምቶ ጥበብ የምዕራብ ጅራፍ ዛሬ
አዘዘው በጥብቅ የዘመኑን ዕውቀት መረሬ
እንዳያርሰው በቀና ልቡና ልጅሽ ገበሬ
እሱም ትእዛዝሽን ሰምቶ
ይነዳው ጀመር በኃይል የምዕራብን ስልት በሬ
ጆሮሽሂ ምድረ ኤርትራ የዓለም ሥልጣኔን ወሬ
ሰምቶ ያሳየዋል ለብሩህ ዐይንሽ ምድረ ትግሬ
ድንገት ቢጥለኝ እኔም አንክሮ ጥበባት እግሬ
ተመለስሁ በማለዳ የጆሮሽን ጌጥ ሳደንቅ አድሬ ።

ምዕራፍ ፫ ጐጃም (አንደበት)

መ ግ ለ ጫ ።

በማርና በወተት በእህልና በከብት ከኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች ሁሉ ይበልጣል ተብሎ የሚገመተው ጐጃም ነው ። ዛፋም ፡ ሣራም ፡ ወንዛም ፡ ዱራም ነው ፤ በጋ የሚ ደርቅ ወንዝ የለበትም ሜዳውና ተራራው ዘለዓለም ልምላሜ አይለየውም ፤ ኮንካ መ ሬት የለበትም ። ከከፋ ፡ ከወለጋ ከኢሉባቦር ደኖች የሚወዳደሩ ጫካዎች በጉታና በመተከል ይገኛሉ ። ማሩ ዘይንተረፍ ወተቱና ቅቤው ዝልኪ ምልኪ ነው ፤ ያብዛኛው ሕዝብ ኑሮ በግብርና ነው ። ሰው በተፈጥሮው ዐዋቂና ጀግና ሩኅሩኅና ለጋስ ነው ። ሀገርዋ የመጻሕፍት መፈታቻ የቅኔ መፈጠሪያ ናት ።

ካህን ፡ ጨዋ ፡ መኰንን ፡ ወይዘሮ ፡ ከተሜ ፡ ባላገር ፡ ጌታ ፡ ሎሌ ፡ ሳይለይ በመላ ሕዝቡ የሚነጋገረው በቅኔ ስለሆነ ከደምበር ከተቀመጡት ሽማግሎች አንሥቶ ከበረት ላም እስከሚያራክቡት እረኞች ድረስ የሚጫወቱበት የንግግር ስልት ኅብር ፡ ውስጠ ወይራ ፡ ሰም ለበስ ወዘተ ነው ልቅሶና ዘፈኑም ቅኔ ነው ፡ አንደበትም የተባለበት ዋና